# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومــو

Gaafa: 04-03-2013 تاريخ
Date:

Lakk.: 03/stm-abo/2013 رقم
No.:


## *ጃራ ኣባገዳ በክብር ሲታወስ ይኖራል*

### *(የታላቁ ታጋይ ጃራ ኣባገዳን ዜና እረፍት ኣስመልክቶ የኦነግ መግለጫ)*

ከኦሮሞ ነጻነት ትግል ኣንጋፋ ኣመራር መካከል ኣንዱ የሆነው ጃራ ኣባገዳ ለረጅም ጊዜ ታሞ በህክምና ሲረዳ ከቆየ በሁዋላ ከዚህ ኣለም በሞት መለየቱ ኦሮምያ ውስጥና ውጭ በሚገኙ የኦሮሞ ብሄርተኞችና የትግሉ ወዳጆች ዘንድ የተሰማው ከጥልቅ ሃዘን ጋር ነው።

በሰፊው ኦሮምያ የትጥቅ ትግል ኣጀማመር ታሪክ ውስጥ የጃራ ኣባገዳ ኣስተዋጽኦ የጎላ ስፍራ ያለው ነው። በምስራቅ ኦሮምያ የትጥቅ ትግል እንዲጀመር ለማስቻል በደቡብ ምስራቅ ኦሮምያ በወቅቱ ሲካሄድ የነበረውን የትጥቅ ኣመጽ ጋር በመቀናጀትና ከዚያም ያለፈ የትጥቅ እገዛ ለማስገኘት እስከ ሶማሊያና መካከለኛው ምስራቅ ድረስ እልህ ኣስጨራሽ የሆነ ኣድካሚ ጉዞ ኣድርጎኣል። ከመካከለኛው ምስራቅ መልስ ሶማሊያ ውስጥ ለኣምስት ኣመታት ታስሮ የሰቆቃ ጊዜ ኣሳለፈ። ከእስር ሲፈታም የኦሮሞን ህዝብ የነጻነት ትግል ኣስተማማኝ መሰረት ላይ ለመገንባት ካለው ጽኑ ምኞት የተነሳ ታጥቆ ወደ ምስራቅ ኦሮምያ በመመለስ ለትግል ያለውን የማያወላውል ቁርጠኝነት ኣስመሰከረ። ጃራ ኣባገዳ በቀጣናው መንግስታትና ሌሎች ሃይሎች የሚቃጣበትን ጥቃት በብቃት ለመመከትና የቆመለትን ኣላማ ከግቡ ለማድረስ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ በጽናት መቆሙ በሁሉም የኦሮሞ ብሄርተኞች ዘንድ በኣርኣያነት ሲዘከር የሚኖር ነው።

ከዚህም ሌላ ቀደም ሲል የኦሮምያ ነጻነት እስላማዊ ግንባር (IFLO) ሲባል በቆየውና ኣሁን የነጻ ኦሮምያ ግንባር (FIDO) ተብሎ በሚጠራው እሱ በሚመራ ድርጅትና በኦነግ መካከል የእርቅ ውይይት በተካሄደበት ወቅት ከፍተኛ የተግባቢነት ኣቁዋም ኣሳይቷል። በ2000 ኣ.ም. በኦሮሞ ታጋይ ድርጅቶች መካከል የነበረውን ልዩነት ለማስቀረት በተደረገው እንቅስቃሴም ገንቢ ሚና በመጫወቱ ይታወሳል። ይህም በወቅቱ የኦሮምያ ነጻነት ሃይሎች ኣንድነት (ULFO) እውን ኣንዲሆን ያገዘ ነበር።

እኛ እንደ ኦነግ በዚህ ኣንጋፋ ታጋይ ዜና እረፍት የተሰማንን ጥቅል ሃዘን ለቤተሰቦቹ፥ ለFIDO ኣባላት እንዲሁም በሃገር ቤትና በውጪው ኣለም ለሚገኘው የኦሮሞ ህዝብና ወዳጆቹ በሙሉ ስንገልጽ ጃራ እስከ መጨረሻዋ የህይወት ዘመኑ የታገለለትን የኦሮምያ ነጻነት ኣላማ ከግቡ ለማድረስ ቃላችንን በማደስ ጭምር ይሆናል። በኣንጋፋው ታጋይ ጃራ ኣባገዳ ዜና እረፍት ያዘኑ የኦሮሞ ብሄርተኞች በሙሉ ቅስማቸው እንዳይሰበርና ኣንጋፋው ታጋይ በህይወት ዘመኑ በሙሉ መስዋእትነት የከፈለለት የህዝባችን ፍትሃዊ የትግል ኣላማ ከግቡ ይደርስ ዘንድ ቁርጠኝነታችሁን እንድታረጋግጡ ጥሪ ኣናስተላልፋለን።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!
ታጋይ ይወድቃል፥ ትግል ይቀጥላል!
የኦሮሞ ነጻነት ግንባር
መጋቢት 4 ቀን 2013


P. O. Box 6973 Asmara, Eritrea |Tel 2911 153848 | *www.oromoliberationfront.org*